# የ‹‹አይቻልም›› መንፈስ የተሰበረበት ጊዜ

***የሺህ አመቱን ድንቅ ሥራ ተመለከቱ***

***ከተጀመረው ይልቅ፤ የሚጀመረው ያጓጓል***

***ጓዶች - የጭብጡን አፅኑ፤ ከፊት ላለው ዘርጉ***

***ቀጥሉ! ቀጥሉ! ቀጥሉ!***

***በአሜን ተፈሪ***

*እና አንዳንዴ፣ ያለፈ ሥራችንን ሳስታውሰው ትዝ ሲለኝ፣*

*ከተጀመረው ነገር ይልቅ፣ የሚጀመረው ነው እሚያጓጓኝ፣*

*(ፓሮዲ)*

ይህ የዜማ ጊዜ ነው፡፡ የህዳሴ መዝሙር የሚዘምርበት ዘመን፡፡ ይህ የመደነቅ ጊዜ ነው፡፡ እጃችንን አፋችን ላይ ጭነን ‹‹ይኽ ተዓምር ነው!›› እያልን የምንደመምበት ዘመን ነው፡፡ ይህ የ‹‹አይቻልም›› መንፈስ የተሰበረበት ጊዜ ነው፡፡ በራስ የመተማመንም ዘመን ነው፡፡ ይህ የብስለት ጊዜ ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን የትንሳዔ ዘመን ነው፡፡ ትናንት፤ በሙት ቀለም ‹‹ወደዚህ የምትገቡ፤ ተስፋ ማድረግን አቁሙ!›› በሚል በዘመን ደጃፍ ላይ የተፃፈው ቃል፤ ዛሬ ‹‹ወደዚህ የምትገቡ፤ ተስፋ ማድረግን አብዙ!›› በሚል በህያው ቀለም በተፃፈ ቃል ተተክቷል፡፡ ይህን የተስፋ መልዕክት ካወጁት ጉዳዮች መካከል፤ በዚህ ሣምንት ያየነው የስልጣን ቅብብሎሽ አንዱ ነው፡፡

ተስፋችንን በደሙ እና በላቡ የሰራው ባለ ራዕዩ መሪ፤ ‹‹እኛው አናፂ፤ እኛው ግንበኛ፤ እኛው መሐንዲስ የሆንንበት፤ የህዳሴ ጉዟችን ባለቤቶችም እኛው መሆናችንን የመሰከረ፤ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታችን… ወይም አቅጣጫ አመላካች ኮከባችን ነው›› ሲል የጠቀሰውና በእግሩ የተተኩት አዲሱ ጠ/ሚ ኃይለ ማሪያም ደሳለኝም ‹‹የባንዲራ ፕሮጀክታችን›› በማለት የገለፁት የህዳሴው ግድብ፤ ያለው አንድ ፋይዳ በ‹‹በአይቻልም መንፈስ›› ተጋርዶ የቆየውን የትንሣዔ ጮራ መግለጥ ነው፡፡ ይህ ግድብ፤ ለዓመታት በየዘርፉ የተካሄደው የለውጥ እንቅስቃሴ ያስገኘውን ቁሳዊ እና ህሊናዊ ውጤት ማህፀን አድርጎ የተወለደ ፕሮጀክት ነው፡፡ በታላቁ የህዳሴ ግድብ ተምሳሌታዊ አብነት የተገለጠው ይህ የህዳሴ መንፈስ፤ ገና በየዘርፉ እየጎላ የሚወጣና የሚገለጥ የወደፊቷ ‹‹ኢትዮጵያ አቅጣጫ አመላካች ኮከብ›› ነው፡፡

ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ መጠቀስ የሚገባው አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም፤ ከሦስት ወራት በፊት አንድ የህክምና ባለ ሙያ በተወካዮች ምክር ቤት በተዘጋጀ አንድ የሽልማት ሥነ ስርዓት ላይ የተናገሩት ቃል ነው፡፡ እንዲህ አሉ፤ ‹‹ከፍተኛ የቀዶ ጥገና ጥበብ የሚጠይቅ የጤና ችግር ያለባት ወጣት ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መጣች፡፡ በውጭ ለሚገኙ የሙያ ባልደረቦቻችን ስለ ችግሩ ስንነግራቸው፤ ሄሊኮፕተር ይዘን እንምጣና በሽተኛዋን እንውሰዳት አሉን፡፡ እኛ ግን ህክምናው እዚሁ መከናወን አለበት አልን፡፡ እናም በኢትዮጵያ ምድር ሊሞከር አይችልም ተብሎ የታሰበውን ህክምና ሰጠን፡፡ ሥራውንም ስኬት አጠናቀቅን›› አሉ፡፡ በተወካዮች ምክር ቤት የተዘጋጀው የሽልማት ሥነ ስርዓት፤ ለዚህ ፈር ቀዳጅ የሆነ የህክምና ሥራ ዕውቅና ለመስጠት የታሰበ ነበር፡፡ ታዲያ የህክምና ባለ ሙያዎቹ አስተባባሪ በወቅቱ የተናገሩት አንድ ቃል የዘመኑን መንፈስ አጉልቶ የሚያሳይ ነበር፡፡ ‹‹በዚህ ሀገር የ‹አይቻልም መንፈስ› ተሰብሯል፡፡ ኢትዮጵያውያን ብቻቸውን አይሞክሩትም ተብሎ ይታሰብ የነበረው እንደ ህዳሴው ግድብ ያለ ፕሮጀክት ከተደፈረ በኋላ፤ በዚህ ሀገር ምንም ነገር ቢሰራ እንዳይገርማችሁ›› አሉ፡፡ ‹‹ተስፋ ማድረግን አቁሙ›› የሚለው ያ የሲዖል ማስታወቂያ፤ ‹‹ተስፋ ማድረግን አብዙ›› በሚል የገነት ማስታወቂያ መተካቱን የሚያውጅ አስተያየት ነው፡፡ የዘመኑ መንፈስ ይኸ ነው፡፡

የአውሮጳ የህዳሴ ወይም የዳግማዊ ልደት (Renascence) ዘመን እንዲህ ያለ መንፈስ የሰፈነበት ዘመን ነበር፡፡ የአውሮጳ የህዳሴ ኃይል፤ አዲስ ቴክኖሎጂ መገኘት አልነበረም፡፡ አዲስ ቴክኖሎጂን የፈጠረው አዲሱ መንፈስ ነበር፡፡ እንዲህ ያለ የተስፋና ‹‹አካባቢዬን መቀየር እችላለሁ›› የሚል መንፈስ የአውሮጳን ህዳሴ ፈጠረው፡፡

የኛም የህዳሴ ኃይል፤ የህዳሴ መንፈስ ኃይል ነው፡፡ ታላቁ መሪ፤ ሰሞኑን እንደገና በቀረበው ***‹‹እንደገና››*** የተሰኘ የቴሌቭዥን ፕሮግራም እንደ ተናገረው፤ ‹‹የህዳሴው መሠረት፤ መንገድና ባቡር አይደለም፡፡ የህዳሴው መሠረት ዜጎች ናቸው›› ብሎ ነበር፡፡ የህዳሴው መሠረት የተባሉትን ዜጎች ለብዙ ዘመናት ቀይዶ ከያዛቸው የ‹‹አይቻልም መንፈስ›› ተላቅቀው፤ የ‹‹ይቻላል›› መንፈስን በጨበጡ ጊዜ ህዳሴው ተፀንሶ ይወለዳል፡፡ በዚህ ረገድ ካየነው፤ አሁን በኢትዮጵያ የተመለከትነው የሥልጣን ቅብብሎሽ ተዐምራዊነቱ ሊቀንስ ይዳዳዋል፡፡ ግን ፋታ ሳይሰጥ በፍጥነት በሚመጣ ሌላ የማሳሰቢያ ድምፅ ተዐምራዊ ማዕረጉን መልሶ ያስጠብቃል፡፡ የኢትዮጵያ የሁለት *ሻመት*[1] ታሪክ ማሳሰቢያውን ይዞ ይመጣል፡፡ ከሺህ ዓመታት በኋላ ያገኘነው ይህ የሚያሳሳ ተስፋ በታሪክ አሽክላ ተጠልፎ እንዳይወድቅ መስጋት እንጀምራለን፡፡

ከአንድ ወር በፊት ‹‹ብሔራዊ ህሊናችንን›› ያናወጠው ከባድ መርዶ በዚያ መጠን ያስደነገጠን፤ ዕድሜ ዘመኑን ሙሉ ሀገሩን ከድህነትና ከኋላቀርነት ለማውጣት ያለ ዕረፍት ሲታገል የቆየው ታላቁ መሪያችን በመሞቱ ብቻ ሳይሆን፤ እርሱ የለኮሰውና በስስት የምንመለከተው የተስፋ ብርሃን እንዳይጠፋ በመጨነቅ ነው፡፡ የለመለመው  ሀገራዊ የተስፋ ቡቃያ እንዳይመክን፤ ቦግ ብሎ የበራው ታላቅ የለውጥ ኃይል እንዳይከስም በመስጋት ነው፡፡

---

[1] ሺህ ዓመት ወይም ሚሊኒየም ለማለት ነው፡፡ የእኛ ጋዜጠኞች ‹‹የሚሊኒየም ግቦች›› የሚሉዋን፤ የምዕተ ዓመቱ ግቦች ብለው ይተረጉሙታል፡፡ ስህተት ነው፡፡ ምዕተ ዓመት ሲል፤ መቶ ዓመት ለማለት ነው – እንግሊዝኛው ሴንቸሪ ይለዋል፡፡ ሚሊኒየም ደግሞ ሺህ ዓመት ነው፡፡

በጊዜው፣ መርዶው በተቀጣጠለው የህዳሴ መንፈስ ላይ የተጋረጠ አደጋ ሆኖ ታይቶኝ ነበር፡፡ እየቆየ፣ ተስፋና ተስፋ መቁረጥ ደባል የሆኑት ስሜት ነገሡብኝ፡፡ አስቀድሞም፣ ‹‹የሀገራችን ሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ግስጋሴ፣ ገና የማይቀለበስበት ደረጃ ላይ አልደረሰም›› የሚል፣ እያሰለሰ የሚመጣ ስጋት ያድርብኝ ነበር፡፡

ኢትዮጵያውያን፣ ከሌላው የዓለም ህዝብ የተሻለ እንጂ የማያንስ የልማት ዕድልና አቅም እንዳላቸው አስባለሁ -ታሪክን ተገን አድርጌ፡፡ በዛው መጠን ደግሞ ስጋት ነበረኝ - አሁንም ታሪክ አይቼ፡፡

ይኸ ህዝብ፣ ቢያንስ የሦስት ሺህ ዓመታት መንግስታዊ ታሪክ ያለው ህዝብ ነው፡፡ ከሦስት ሻመት በላይ ሀገራዊ ነጻነቱን ጠብቆ የቆየ ህዝብም ነው፡፡ ከስልጣኔና ብልፅግና ዙፋን ከወጣ በኋላ፣ ከኋላ ቀርነትና ከድህነትና የመጨረሻ አዘቅት የወደቀም ነው፡፡ ታሪኩ ይህን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ባለፈው አንድ ሺህ ዓመት ውስጥ ፈጣን የቁልቁለት ጉዞ ለመጓዝ  ተገድዷል፡፡ በዚህም የውድቀት ጉዞ ውስጥ አልፎ አልፎ ቆም እያለ ተዓምር ይሰራል፡፡ ግን የቁልቁለት ጉዞውን የሚገታ እርምጃ ማድረግ አልቻለም፡፡ ከሻመቱ ውስጥ የሚበዛውን  ዘመን በጦርነት (በውስጥ እና በውጭ)፣ እንዲሁም በከፋ ድህነት ሲማቅቅ ቆይቷል፡፡ ግን ከጦርነቱ ትንሽ ፋታ ሲያገኝ፣ አቧራውን አራግፎ ብድግ ይላል፡፡ በጦርነት ተጠምዶ እየወደቀ፣ ደግሞ - ደግሞ እየተነሳ ተጉዟል፡፡ ይህ ሁኔታ ተስፋ የሚያሳድረውን ያህል፣ ተስፋን ጠብቆ ዘላቂ የማድረግ ችግር (ሰበቡን በውጭ ከማላከክ ርቀን ካየነው) እንዳለበት የሚያመለክት ሆኖ ስጋት ይጎትታል፡፡

ታሪካችን ገና በውል አይታወቅም፡፡ የታሪክ ጥናት እና ምርመራችንም ከአውሮፓ ምሁራን ተፅዕኖ አልተላለቀም፡፡ አሁን የምናያቸው እንደ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ፋሲለደስ፣ ጀጎል፣ ጢያ ወዘተ... ያሉት ቅርሶች ሊኖረን ከሚችለው የቅርስ ሀብት እጅግ ጥቂቶቹ እንደሆኑ አስባለሁ፡፡  ከመሬት በታች የሚገኘው ብዙ ድንቅ ገና አልወጣም፡፡ ለእኛም ሆነ ለዓለም ህዝብ ትንግርት የሚሆኑ ብዙ ቅርሶች ገና ከመሬት በታች ናቸው፡፡ አንዳንድ ነገሮች አሁን መውጣት ጀምረዋል፡፡ እየተካሄዱ ያሉና ገና ይፋ ያልተደረጉ የአርኪዮሎጂ ሥራ ግኝቶች ለሌላ ድንቅ እንድንዘጋጅ የሚገፋፉን ናቸው፡፡

ከመነሻዬ በጠቀስኩት የኢቴቪ ፕሮግራም፣ ፕሮፌሰር እንድሪያስ፣ ‹‹ትናንት ትልቅ መሆን፣ ከኋላ ቀርነት አያድንም›› እንዳሉት፣ በአንደኛው ሻመት መጀመሪያ የነበረው ታላቅነታችን ወደ ኋላ በመጡት ምዕተ ዓመታት ከደረሰብን ውድቀት አልጠበቀንም፡፡ ስለዚህ ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ  እንዳሉት፣ ‹‹በአንድ ወቅት በዓለም የስልጣኔ ጠርዝ ላይ የነበረው ይህ ህዝብ፣ ከዓለም የድህነት ጠርዝ ላይ ወደቀ፡፡››

እናም ታሪካችንን መለስ ብለን ስናየው፣ የውድቀቱ ልክ፣ ፍጥነትና መስፋፋት ጉድ ነው፡፡ ከላሊበላ ወዲህ ባሉት ወደ ዘጠኝ መቶ ዓመታት፣ የላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ ፋሲለደስን ቤተ መንግስትና፣ የጀጎል ግንብን ሰርተናል፡፡ ይህ በሀገራችን ብቅ እያለ የሚጠፋውን የሥልጣኔ ሻማ ያመለክተናል፡፡ እናም ይህ ህዝብ አጋጣሚ ሲያገኝ ከወደቀበት ብድግ ብሎ ይነሳል፡፡ ግን የለኮሰውን ሻማ ከአደጋ ጠብቆ ለረጅም ዘመን የመዝለቅ ተደጋጋሚ ችግር ይስተዋልበታል፡፡

እናም፤ አሁን በእኛ ዘመን አዲስ ተስፋ ሲፈጠር ሳይ፤ የተስፋው ዘላቂነት አሳስቦኛል፡፡ ይህ ህዝብ ትንሽ ሰላም ሲያገኝ ከወደቀበት ተነስቶ በእግሩ መቆም እንደሚችል ከቶም አልጠራጠርም፡፡ ግን የተስፋውን ቡቃያ በሆነ ችግር አያጠፋውም የሚል መተማመን አላሳደረብኝም፡፡

ስለዚህ፤ የጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ህልፈተ ህይወት የሰማሁት በታላቅ ድንጋጤ፣ ስጋት እና ጭንቀት ነበር፡፡ እንደ መብረቅ ድንገት የወረደው ያ መርዶ ካከረረው የሀዘን ስሜት እንደ ነቃሁ፤ ሀሳብና ልቤ የተጠመደው፤ ‹‹የተፈጠረው ይህ አደጋ ጨርሶ ተስፋችንን እንዳያከስመው በበኩሌ ምን ማድረግ እችላለሁ›› በሚል ጥያቄ ላይ ነበር፡፡ ‹‹እስከዚህ መጥተናል፡፡ የተስፋ ጭላንጭልንም አይተናል፡፡ ታዲያ የእስካሁኑን ድል እንዴት ጠብቀን መጓዝ እንችላለን›› ብዬ ራሴን ጠየቅኩ፡፡

በዚህ መጠን፤ ራሴን ለአንድ ማህበራዊ ኃላፊነት እና ዓላማ፤ ፍጹም በሆነ ልብ አዘጋጅቼ አላውቅም፡፡ ያ የመርዶ ቀን በዚህ ሁኔታ አለፈ፡፡ ምሽት ላይ የታላቁ መሪያችን አስከሬን ይገባል፡፡ የአቀባበል ሥነ ስርዓቱን መከታተል ጀመርኩ፡፡ አሁንም ስጋት እንደ ተጫነኝ ነው፡፡ ዝናብ እና እንባ ያበሰበሰውን አስከሬን የሚጠባበቅ የአዲስ አበባ ህዝብ ሳይ እጅግ አዘንኩ፡፡ አስከሬኑ ከአውሮፕላን ማረፊያ ወጥቶ ከህዝቡ ዘንድ ከደረሰ በኋላ የተፈጠረው ትዕይንት፤ ፍፁም ያላሰብኩት ነበር፡፡ እስካሁን ከምን ሊመደብ እንደሚችል ያላወቅኩት አንዳች ስሜት አጥለቀለቀኝ፡፡ ልቤ የብዙ ስሜቶችና ሀሳቦች ‹‹ፍኖተ ሀሊብ›› (Milk way) ሆነ፡፡ በአቀባበሉ ሥነ-ስርዓት የተመለከትኩት ትዕይንት፤ ሀዘን እና ለቅሶ ሲመስል፤ ፅናትና አስተዋይነት እየሆነብኝ፤ መረበሽ እና ግራ መጋባት ሲመስል፤ ማወቅና ማሳወቅ እየሆነብኝ፤ የሁከት እና የረብሻ የመጀመሪያ ምዕራፍ እየመሰለኝ፤ የማይናወፅ የሰላም እና የፍቅር ኃይል እየሆነብኝ፤ ሞትን አጅበን የምንሄድ ሲመስለኝ፤ ህይወትን የሞሸርን መሆኑን ተሰማኝ፡፡ ሌላም… ሌላም…

የዚህ ታላቅ ህዝብ አባል የመሆን ስሜት አኮራኝ፡፡ ይኸ ህዝብ፤ የሚሰራውን አሳምሮ የሚያውቅ ህዝብ መሆኑ ተሰማኝ፡፡ ትልቅ፣ ትንሽ፣ ሴት ወንድ የተማረ- ያልተማረ ሳይባል፤ ሁሉም ሰው የሚናገረውን ስሰማ፤ ጠቅላላ ህዝቡ ፈላስፋ፣ ገጣሚ፣ የፖለቲካ ምሁርና ስትራቴጂስት ወዘተ ሆኖ ታየኝ፡፡ ህዝቡ ፍፁም ፍትሃዊ ዳኛ መሆኑን ተመለከትኩኝ፡፡

አልፎ- አልፎ ይሁን እንጂ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በአስገራሚ መጠን ጨዋ እና ፍትሐዊ ህዝብ በመሆኑን እያሰብኩ ተደንቄ አውቃለሁ፡፡ ሆኖም በአሁኑ ልክ በአድናቆትና በአክብሮት ተመልክቼው አላውቅም፡፡ ህዝቡ፤ ከመንግስት ተቋማት፣ ከፀጥታ፣ ከመከላከያ እና የፖለቲካ ኃይሎች ወይም ሥልጣናት አስቀድሞ፤ ‹‹የራሱን ዕድል በራሱ›› ሲወስን ያየሁበት ልዩ አጋጣሚ ነበር - ያ ምሽት፡፡

ህዝቡ፤ በቅፅበት ከተመልካችነት ወደ ተዋናይነት ሲሸጋገር፤ አዕምሮን ከስሜት አመዛዝኖ ይዞ ሲጓዝ ተመለከትኩ፡፡ ሰፊ ራዕይ አየ፡፡ ራዕዩን ተረጎመ፡፡ ‹‹ጀግና አይሞትም›› አለ፡፡ ‹‹ዘፈን›› ከለቅሶ ተቀላቀለ፡፡ ሙሾ ይመስላል፤ መዝሙር ነው፡፡ መረታት ይመስላል፤ ፅናት ነው፡፡ መታወክ ይመስላል፤ ሰላም ነው፡፡ ዝርው ቃል ይመስላል፤ ግጥም ነው፡፡ ሁኔታውን በወርድ፣ በቁመትና በርዝመት የሚመጥን ወይም ሌላን አገላለፅ ሁሉ ዲዳ የሚያደርግ ቃል ተናገረ፤ ‹‹ጀግና አይሞትም!›› አለ፡፡

‹‹ጀግና አይሞትም!››፤ ትናንትን፣ ዛሬን እና ነገን የሚገልጥ የታላቅ ህዝብ ታላቅ ቅኔ ነው፡፡ በዚያች ቃል ሰላሙን አፀና፤ ጉዞውን ተለመ፤ ፍላጎቱን ለጠላትም - ለወዳጅም በግልፅ አዋጀ፡፡ በዚያ ምሽት፤ ውቂያኖሳዊ ማዕበልን ሁሉ እንደ ስኒ ማዕበል የሚያስቆጥር ኃይል ተገለጠ፡፡ ህዝቡ መሪ እንጂ ተመሪ አለመሆኑን አረጋገጠ፡፡ ሰላሙን የሚጠብቅ ዘብ አልፈለገም፡፡ ከእርሱ በላይ ማን ዘብ አለ፡፡ መንገድ አመላካች አልፈለገም፡፡ በእርሱ ራሱ መንገድ ሆነ፡፡ ህዝብ እና ቤተ መንግስት ተቀላቀለ፡፡ መለያየታቸው ቀረ፡፡ አንዱ ከሌላው፤ በቋንቋ፣ በብሔር፣ በሐይማኖት፣ በዕድሜ፣ በፆታ፣ በአመለካከት መለያየቱ እንደ ጉም በኖ የጠፋ መሰለ፡፡ የተፈጥሮ ወግ ተጣሰ፡፡ የልዩነት አጥር ፈረሰ፡፡ አንድ ሆነ፡፡ አንድ!

ህዝብ ሲሆን፤ አንድ ሰው አከለ፡፡ አንድ ሰው ሲሆን ህዝብ አከለ፡፡ ኢትዮጵያ፤ የአንድ ቤተሰብ አንድ ድንኳን ሆነች፡፡ በህይወቱ ያለ ዕረፍት የሰራው ታላቁ መሪ፤ በሞቱም ሥራውን አላቋረጠም፡፡ ይኸ ሰው አሁንም አላረፈም፡፡ ሞተ ያልነው መሪ ህያው ሆነ፡፡ በዘመን የተወሰነ የሚመስለው ጀግና፤ የዘመንን ወሰን የሚያልፍ ምትሃት ሆነ፡፡ ትውልዶችን እየተሻገረ ዜጎችን ለሥራ የሚያነሳሳ አንድ የመንፈስ ኃይል ሆኖ ቁጭ አለ፡፡ በዘመናት የማይዘነጋ ትንግርት፣ መጪዎቹን ትውልዶች እና የየትውልዱን መሪዎች በመንፈስም የሚያንፅ ኃይል ሆኖ እንደሚዘልቅ አመለከተ፡፡

ታላቁ መሪያችን፤ በእርሱ የዕድሜ ዘመን የሚመጠን የውሸት ሰላም የተወልን አይደለም፡፡ በእርሱ ህልፈት የሚናድ የድቡሽት ላይ ቤት አልሰራም፡፡ እርሱን የፈጠረ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ሰጥቶን፣ ራዕይ አውርሶን፣ የልማት ቅርስ ትቶልን አለፈ፡፡

እርሱ ባያየውም፤ ለህዝብ ከልብ መስራት የሚያስገኘውን ህዝባዊ ክብር ተተኪ ጓዶቹ አይተዋል፡፡ የህዝቡን ውለታ አክባሪነት ተመልክተዋል፡፡ ለእርሱ የተቸረው ፍቅርና ክብር የእነርሱም እንደሆነ ይረዳሉ ብዬ አስባለሁ፡፡ ‹‹መስራች አባቶች›› በሚል ስማቸው በታሪክ ማህደር እንደሚሰፍር አምናለሁ፡፡

ጠ/ሚ መለስ በሐሳብ አፍላቂነት የሚወደስ ታጋይ ነው፡፡ በህዝባዊ ትግል ሂደት ተሰርቶ የወጣ ታላቅ መሪ ነው፡፡ በእሳት ተፈትኖ - ነጥሮ በወጣ ድርጅት ውስጥ ታቅፎ እያደገ የሄደ ታጋይ ነው፡፡ ከሀገር አልፎ፤ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ዕውቅናን ያተረፈ ኢትዮጵያዊ መሪ ነው፡፡ ታዲያ ከዚህ ታላቅ መሪ የሰላ ህሊና የሚፈልቁ ትላልቅ ሐሳቦች ሁሉ፤ ሕይወት የሚለውጥ ኃይል ከመሆናቸው በፊት፤ በጓዶቹ አዕምሮ መመዘን፣ መደገፍ፣ መከበርና እውቅና ማግኘት ያሻቸዋል፡፡ በዚህ ሂደት ወይም በድርጅታዊ የሐሳብ ትግል ጥራታቸው ይሻሻላል፡፡ ይጎለብታል፡፡ ሁሌም ከአንድ ህሊና የፈለቀ እውነት፤ በሌላ ህሊና ተዳኝቶ መረጋገጥ ይፈልጋል፡፡ ተዳኝቶ እውቅና ሲያገኝ ወይም የድርጅት ሐሳብ ሲሆን፤ ከዚያም በህዝቡ ልብ ተቀባይነት ሲቸረው ቁሳካል ይሆናል፡፡ ሀገርን የሚለውጥ ኃይል ይሆናል፡፡

የመለስን ታላቅነት ተረድተው፣ በተራ ስሜትና ፉክክር ባለ ራዕዩን የትግል ጓዳቸውን ሳያደናቅፉ፤ የአመራር መንበሩን ባልተቋረጠ ሁኔታ እንዲይዝ ያደረጉ ጓዶች ከእርሱ እኩል ከበሬታ የሚያገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ በህዝባዊ ፍቅር ታንጸው ያደጉ፣ በእሳት ተፈትነው የወጡ ታጋዮች፣ እርሱን አክብረው ለታላቅነቱ የለመለመ ማሳ ሆነዋልና ታላቅ አክብሮት የሚገባቸው ናቸው፡፡ ለህዝብ ባላቸው አክብሮትና ፍቅርም፤ በታላቁ መሪ ልክ

የሚቆሙ ናቸው፡፡ እንደሱው በአንዲት ህዝባዊ ጎጆ ተኮራምተው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ እራፊ ጨርቅ ደርበው፣ በትግል ጎልምሰው፣ የወጡ የህዝብ ልጆች ናቸው፡፡

ህዝብን በእውነት ማገልገል ምን ዓይነት ክብር እንደሚያጎናፅፍ፣ በንድፈ ሐሳብ ሳይሆን በተግባር አስተውለዋል፡፡ እነሱም ህዝቡን አክብረዋል፡፡ ‹‹አሁን ህዝቡ የተሰማውን የሐዘን ስሜት ከማስተናገድ የበለጠ ሥራ የለንም›› ብለዋል፡፡ ሀዘኑን በማስተናገድ ሂደት፣ ከነባር ድርጅታቸው መርህ የወጡ አንዳንድ ሁኔታዎች እንደሚገጥማቸው እገምታለሁ፡፡ ሆኖም፣ ለወቅታዊ ጥልቅ የሀዘን ስሜት ባዕድ የሚያደርግ ቃል ሳይወጣቸው፣ በዛው ልክ ጥንቃቄና ማስተዋል ሳይርቃቸው፣ በተሳካ መንገድ የሀዘን ሥነ ስርዓቱን በማከናወን ታላቅነታቸውን አሳይተዋል፡፡

ነባሮቹ ታጋዮች በሙሉ፣ በአገኙት አጋጣሚ፣ ስሜትን ከአዕምሮ ጎን ማራቅ ለማይወድ ሰው መፅናኛ የሚሆን የተኳለ ሀሳብ ጣል እያደረጉ፣ እግራቸውን ሳይነቅሉ የስሜትና የሀዘኑን ጎርፍ ይሻገሩ እንደ ነበር አይተናል፡፡ በመጨረሻም፣ ታላቅነታቸውን በሚያሳይና ለዚህ ታላቅ ህዝብም ሽልማት በሚሆን ሁኔታ የስልጣን ቅብብሎሹን አጠናቀቁ፡፡ ለዚህም አክብሮታችን ይድረሳቸው፡፡

ታዲያ ይህን የህዝብ መነሳሳት ይዘው የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በመጨረስ ብቻ ሳይሆን፣ ተጨማሪ ድል በማስመዝገብ የመረጣቸውን ህዝብ እንደሚያኮሩት አምናለሁ፡፡ የታላቁን መሪ ድል አብዝተው እንደሚያደምቁትም ቅንጣት አልጠራጠርም፡፡

በዚህ ሂደት፣ ኢትዮጵያ አንድ ልዩ የታሪክ እርምጃ ተራመደች፡፡ ታሪክ የሚያስረዳን፣ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁልጊዜም በጦርነትና በሁከት ወደ ሥልጣን ሲመጡና በተመሳሳይ መንገድ ከሥልጣን ሲወገዱ ነው፡፡ ኢትዮጵያ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፣ የአፄ በጉልበቱ ሀገር ሆና ቆይታለች፡፡ ነገስታቱ ከአልጋ እንደ ወጡ የሥልጣን ተቀናቃኝ የሚሏቸውን ሁሉ (ወንድም - እህት፣ አክስት - አጎት ሳይቀር) ሰብስበው በወህኒ አምባ ያጉራሉ፡፡

በዚህ ሁኔታ፣ ተከታዩ ንጉስ ከቀዳሚው የሚማረው ሳይኖር ሽግግሩ ይቀጥላል፡፡ አንዳንዴም ህፃናት በሞግዚት የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ ሲፈጠር አይተናል፡፡ ሀገሪቱም በዜሮ እየተንፏቀቀች ዘመናት ገፍታለች፡፡ ንጉሱም ከተቀናቃኝ እና ከአመፀኛ እየተዋጋ በድንኳን እየተንከራተተ ሲኖር ቆይቶ ወደ መቃብሩ ይወርዳል፡፡ ሀገሪቱም፣ የባህልና የዕድገት ማዕከል የሚሆን መዲና እንኳን ሳይኖራት፣ እንደ ሱቅ በደረቴ እየዞረ ከሚኖር ንጉስ ጋር ስትንከራተት ዕድሜዋን ገፍታለች፡፡ ይህ ነው፣ የረጅም ዘመን ታሪካችን፡፡

ይህ ሁኔታ፣ ቀዳሚው ለተከታዩ የሚያወርሰው መሠረት የሚያስይዝ አንዳች ነገር ሳይኖር፣ ሁሉም ከባዶ የሚነሳበት መጥፎ ቅርስ ፀንቶ እንዲቆይ አድርጓል፡፡ ህዝቡም ልማትና ዕድገቱ ቀርቶበት፣ በሰላም ውሎ መግባቱን ብቻ፣ ከትልቅ ነገር እንዲቆጥር አድርጎት ቆይቷል፡፡ ስለ ቅብብሎሽ መሥራት ሳይሆን፣ ለማውራት እንኳን አልቻልንም፡፡ ፍላጎትም አልነበረም፡፡ በዚህ ሂደት እንደ ሀገር የምናጣው ብዙ ነው፡፡ አንዱ መሪ ከሌላው አይማርም፡፡ የቀዳሚውን መሪ ደብዛዎች (Legacy) ለማስጠበቅ የሚሰራና ካለፈው ስኬት ስንቅ ይዞ የሚወጣ ብቁ መሪ ማግኘት አንችልም፡፡

በአንድ ትውልድ ስለሚፈፀም ማራቶን ሳይሆን፤ በተከታታይ ትውልዶች ስለካሄድ የዱላ ቅብብሎሽ መነጋገር መጀመር ለኢትዮጵያውን ትልቅ ለውጥ ነው፡፡ አልፎ-አልፎም ቢሆን፤ ቦግ ብሎ ታይቶ የሚከስም ተዐምር መፍጠር ወይም ማራቶን መሮጥ እንዳልቸገረን ታሪክ ይመሰክራል፡፡ ትልቁ ችግራችን የተገኘውን ለውጥ ጠብቆ የመያዝ፤ በተከታታይ ትውልዶች  የሚካሄድ የዱላ ቅብብሎሽ ማድረግ ነው፡፡ አሁን የምናየው ሁኔታ እና በተያዘው ዕቅድ መሠረት የሚከናነው ሥርዓት ያለው የመተካካት ሂደት ኢትዮጵያ ፍፁም እየተለወጠች መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ባለፈው ሣምንት መጨረሻ መስከረም 11፣ 2005 ለአስቸኳይ ስብሰባ የተጠራው የተወካዮች ምክር ቤት የዚህ ትልቅ የታሪክ ክስተት መድረክ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ የታሪክ ጉዞ መሪ ሲሞት ሁሉ ነገር ይፈርሳል፡፡ በግንባር ተሰልፎ በጦርነት ድል የተቀዳጀ ሠራዊት፤ ድንገት መሪው ሞተ ሲሉት በጁ የጨበጠውን ድል ሜዳ ጥሎ ሲፈርስ፤ ከዚያም በስልጣን ሽኩቻ ሲታመስ ነው የምናውቀው፡፡ አሁን የተቀየረው፤ ይህ ታሪክ ነው፡፡ የመጣንበትን መንገድ መለስ ብሎ ለተመለከተ ሰው፤ ይህ ምን ዓይነት እመርታ እንደሆነ በቀላሉ ይገነዘባል፡፡

ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን ሲመጣ የተረከበው፤ ህዝብን አፍኖ ሲገዛና ሲጨፈጭፍ የነበረ ጨካኝ ወታደራዊ ኃይል  ያደቀቃትን ሀገር ነው፡፡ ባዶ ቤትና ካዝና ነው፡፡ ስለዚህ፤ ሀገር የመምራት ሥራውን ሲጀምር ማጣፊያው እንደሚያጥረው እሙን ነው፡፡ ስለዚህ፤ ‹‹ሲያስቡት - ሲያስቡት›› የሚያደክም ፈተና ተጋፈጠ፡፡

ኢህአዴግ የተረከባትን ኢትዮጵያ እና የገጠመውን ፈተና፤ በአንድ አሮጌ ታክሲ እና በሹፌሩ ምሳሌ በግልጥ ይታያል፡፡ ይህች አሮጌ ታክሲ ጎማዋ አልቋል፡፡ ወንበሯ ተቦዳድሶ ሽቦው ወጥቷል፡፡ ባሌስትራዋ ተሰብሮ ታስሯል፡፡ አካሏ በየቦታው ተበይዷል፡፡ ነዳጅ መያዥው ተቀዷል፡፡ መስታወቷ መፍቻ ተወትፎበት በእጅ እየተሳበ ይዘጋል- ይከፈታል፡፡ ሞተሯ በግፊ ይነሳል፡፡ ተሳፋሪዎች ገብተው ተቀምጠዋል፡፡ ትዕግስት የላቸውም ይቸኩላሉ፡፡ ጥድፊያ ነው፡፡ መኪናዋ፤ እንደ ምንም በግፊ ተነሳች፡፡ ሆኖም ጉዞዋ፤ የህዝቡን አጣዳፊ ፍላጎት ሊያረካ የሚችል እንደማይን ግልፅ ነው፡፡ ገና ሲያዩት የሚያስፈራ ዳገት ከፊታቸው ተገትሯል፡፡ ገና ሲያስቡት ያደክማል፡፡

ግን ሲያስቡት - ሲያቡት ደክሟቸው አልተውትም፡፡ የሀገሪቱ ችግር ብዛት፣ የናዳው ፍጥነት፣ የህብረተሰቡ ጥያቄ- ፍላጎት ስፋት፣ የመንግስት አቅም ውሱንነት፣ እርዛት የብርድ ልብሱ አጭርነት የ«አንዱን ሲሉት አንዱ´ አታካችነት… ወጥሮ እያጠራቀቃቸው፤ የሀገሪቱ ነገር መሠረት በሌለው፣ በድቡሽት ላይ የተገነባ ቤት ሆኖ እያስጨነቃቸው፣ ነፋሱ ሲነፍስ ጎርፍ ሲመጣ፤ ያን ቤት ሲመታው፣ ሲወድቅ፤ አወዳደቁም ታላቅ ሲሆን እየታያቸው፤ ይህም እያስፈራቸው… አሮጌ መርከብ ላይ ሆነው አስፈሪው ማዕበል እያንገላታቸው፤ ከፊታቸውም ማጎለቅት የሌለው ውቂያኖስ ተዘርግቶ ዳርቻው እየራቃቸው ተጨንቀዋል፡፡ አቤት ስቃይ!!!

ብዙ ተለፍቶ ቋቱ ባዶ ነው፡፡ የሚያዋክበውና ትኩረት የሚፈልገው ነገር ብዙ ነው፡፡ ማዕበሉ እረፍት የለውም፡፡ ያለ ማቋጥ ከፊታቸው ያነገንጋል፡፡ አንዱን መከራ አልፈው፤ ማዕበሉ ትንሽ ደብ ሲል፤

‹‹እንዳያልፉት የለም፤ ያ- ሁሉ ታለፈ፣ ታጋይ የህዝብ ልጅ፤ በደሙ ባጥንቱ ደማቅ ታሪክ ፃፈ›› ብሎ፤ ለመጽናናት (ለማዜም አይደለም) ፋታ የተገኘ መስሎ ይታይና፤ ያ ደብ ያለው ማዕበል ወዲያው ያነገንጋል፡፡ ደግሞ ተሶርፎ ይፎግላል፡፡ የነብር ጅራት ነው የተያዘው፡፡

ግብግቡ ይቀጥላል፡፡ ላብና ደም ዱብ - ዱብ ይላል፡፡ የመርከቡ ካፒቴን ባህሩ ጸጥ ሲል፤ የጉዞ አቅጣጫ ለመተለም ያቀረቅራል፡፡ ቀን በፀሐይ፤ ሌት በኩራዝ ካርታውን ይመረምራል፡፡ ኮምፓሱን ያያል፤ የአየሩን ሁኔታ ይገመግማል፡፡ አቅል አጥቶ ያን ይኸን እያነሳ ጥሎ፤ በሀሳን ሰመመን ውስጥ ገብቶ፤ የብልጽግና ራዕይ ብልጭ ሲልላት ጩኸትና እሪታ ከራዕዩ ያናጥበዋል፡፡

እረፍት የለውም፡፡ በድግ ይላል፡፡ ‹‹ተነሱ ጓዶች፣ ቀጥሉ.. ቀጥሉ.. ቀጥሉ!›› እያለ ይጣራል፡፡ ሰዎች ‹‹መጥፋታችን ነው! እባክህ አድነን!›› እያሉ ሲጣሩ ይሰማል፡፡ በፍጥነት ወደ ዳርቻው ካልወጣን፣ አንድ ማረፊያ ወደብ ካልተገኘ በደከመችው አሮጌ መርከብ የሚነሳው ትርምስ፤ መርከቧን ሚዛን አሳጥቶ ከማዕበሉ ጋር ተባብሮ፣ ከነፋሱ ጋር ተዳብሎ እንደሚያሰጥማት፤ ተጓገሮቹንም የዓሣ ነባሪ እራት፤ የጉማሬ ቀለብ እንደሚያደርጋቸው ያውቃል፡፡ ብቻ ‹‹ጓዶች ቀጥሉ!- ቀጥሉ- ቀጥሉ!›› ይላል- እንደ ማጅላን ይጣራል፡፡

‹‹አሁን እዚያ ከማያት የወፍ ደሴት ሄጄ፣ ተጓዡን አረጋግቼ፤ እኔም ትንሽ ትንፋሽ ሸምቼ፤ የጉዞ አቅጣጫዬን በደንብ ለይቼ መሄድ ይሻለኝ ይሆን›› ሲል ይጠይቃል፡፡ ደግሞ፤ የወፍ ደሴቱ ያለበት ከዋናው የጉዞ መስመር የሚገነጠል በመሆኑ ኪሳራ ሆኖ ይታየዋል፡፡

‹‹የለም! አሁን እዚያ ደርሼ እንደገና ወደ ጉዞ መስመር ለመግባት የሚፈጀው ጊዜ፤ የሚጠፋው ጉልበት፣ የሚደረገውም ትግል እንዲሁ የባከነ ሀብትና ጉልበት ሆኖ ይቀራል፡፡ ለዋናው ጉዞ ሊውል የሚችል የስስት ሀብት በከንቱ ይባክናል!›› እያለ ይዋልላል፡፡ በዚያ መሐል ‹‹ እባክህ አድነን! አለቅን! ኸረ ስለ ፈጠረህ!›› ይሉታል፤ በወቀሳና በመማፀን ድምፅ፡፡ ‹‹የለም ወደ ዋናው መሬት የሚወስደውን መንገድ መልቀቅ የለብኝም›› ብሎ አምኖ ወስኖ፤ የመንገዱን ርዝመት፣ የተናጣቂውን አውሬ ግሳት፤ እየተመለከተ እየሰማ፤ ሲያስበው - ሲያስበው ሊደክመው እያለ፤ መቃብር ፈንቅሎ እንደ መነሳት ባለ መንፈሳዊ ኃይል መንፈስን የሚያዝለውን ሀሳብ ወዲያ አሽቀንጥሮ ጥሎ ለመሄድ ሲነሳ፤ ‹‹እባክህ አድነን!›› የሚለው ተማፃኝ ድምፅ ሆዱን እያንቦጫቦጨው ጉዞውን ተግ ያደርግና ‹‹የለም አያዋጣም መልፈስፈስ አይገባም፡፡ የነብሩን ጅራት መልቀቅ አልችልም›› ብሎ ወደ ዋናው ምድር ጉዞውን ይቀጥላል፡፡ ‹‹ፉና- ቤት›› አልታይ ብሎት ተቸግሯል፡፡ ግን መቆም አልፈለገም፡፡ ‹‹በመሄድ ከወደቡ ይደርሳል፡፡ መቆም ጊዜ ይሰርቃል፤ ክረምቱን ያቃርባል›› በማለት ጨክኖ ጉዞውን ይቀጥላል፡፡ የነፋስ ሽራውን የሚያወላግዱ ባህርተኞችን፤ ከመጋዘን የሚሰርቁ አንዳንድ ቀዛፊዎችን እየተፋለመ፤ የዋና ጉዞ መስመሩን እንዳይለቅ እየተጠነቀቀ፤ ተጓገሮችን አረጋግቶ ‹‹ጓዶች- ቀጥሉ!- ቀጥሉ! ቀጥሉ!›› ሲል ይጮኻል፡፡ ከባህር ወንበዴዎች ጋር ጦርነት ይገጥማል፡፡ የተበጠሰ ገመድ ይቀጥላል፡፡ ባህርተኛውን ሰብስቦ፤ ‹‹ይህን ባህር ሰንጥቀን በፍጥነት ካልተጓዝን አደጋ ይከተላል›› ይላል፡፡

አንዳንድ ባህረኞች ይሞግታሉ፡፡ አዛኝ- ቅቤ አንጓች የሆኑ ቡድኖች ‹‹በዚህ ዓይነት ጉዞ፤ የትም አንደርስም›› ይሉታል፡፡ ‹‹አሁን ወደ ወፎች ደሴት ሄደን፤ እዛ ትንሽ አረፍ ብለን፤ ስንቅ የሚሆን እህል ካገኘንም

ሽምተን፤ ስንቃችንን አጠናክረን፤ በአቋራጭ መንገድ መጓዝ ይቻላል›› ይሉታል፡፡ በሂሊኮፕተር እየበረሩ መጥተው፤ የሚሄዱ የውጭ ሀገር ሰዎች የሚሉትን እየጠቃቀሱ ይሞግቱታል፡፡

‹‹ይኸ ደሴት እንዲህ እንደምታዩት ቅርብ አይደለም፡፡ ይኸ ቢያንስ የስድስት ወር መንገድ ይሆናል፡፡ መንገዱ አደገኛ የባህር አውሬዎች፤ መጥፎ የባህር ወንበዴዎች፤ መተላለፊያ ነው፡፡ ደሴቱም እየነሱ ፌርማታ ነው፡፡ አቋራጭም አይደለም፡፡ ግን ወደ ዋናው ምድር የምናደርገውን ጉዞ የሚያቋርጥ በመሆኑ፤ አቋራጭ ሊባል ይችላል፡፡ ጉዞአችን ወደ ተስፋይቱ ምድር እንጂ ደረቅ ጣቢያ ወደ ሆነ የወፎች ደሴት አይደለም›› ይላቸዋል፡፡

እነሱም ቃላቸውን አፅንተው ይከራከሩሉታል፡፡ እርሱም ይመልሳል፤ ‹‹አይደለም፡፡ the shortest distance between two points is the straight-line ሲሉ ሰምታችሁ ይሆናል፡፡ 2 ሲደመር 2 -እኩል ይሆናል- 4፤ ማለት በሂሳብ ስሌት ትክክል ነው፡፡ በማህበራዊ ሳይንስ ወይም ፍልስፍና ልክ ላይሆን ይችላል፡፡ the shortest distance between two points is not the straight-line›› ይላል፡፡ ደግሞም፤ ከመርከበኞቹ እንዲህ ዓይነት ሰዎች በመኖራቸው ሀዘን ይሰማዋል፡፡ ግን ስሜቱን አልተናገረም፡፡ ከቀጥተኛው ጉዞም አልወጣም፡፡

‹‹ጓዶች፤ ቀጥሉ!- ቀጥሉ!- ቀጥሉ!›› ሲል ሰማሁት፡፡ ካፒቴኑ ወጀቡን፣ ውሽንፍሩን፣ ሁከቱን ጩኸቱን ተቋቁሞ፤ አሁን በቃት ሰጠመች እያሉ የሚያይዋትን፣ በጦርነት ተቀጥቅጣ የደከመች አሮጌ መርከብ ይዘው፤ ይህን ማኅለቅት የለሽ የሚመስለውን የመከራ ውቂያኖስ ተሻግረው፤ በሩቅ ያለች የብርሃን ነቁጥ ታየች፡፡ ፋና ቤት፡፡ በመርከቡ ያሉ ተጓገቾችና መርከበኞች ‹‹ብራቮ! ብራቮ!›› ሲሉ ጮኹ፣ ዘለሉ፡፡ ተቃቀፉ፡፡ ፈነጠዙ፡፡ ‹‹እንያልፉት የለም! ያ ሁሉ ታለፈ፤ ታጋይ የህዝብ ልጅ፤ በደሙ በላቡ ደማቅ ታሪክ ፃፈ›› የሚለው መዝሙር አስተጋባ፡፡

እውነት፤ ስንቱ ታለፈ፡፡ ታሪክ ዘወር ብለው ሲያዩት እንጂ ሲሰሩትና ሲያልፉበት ትርጉሙ ብዙ አይወቅም፡፡ ግን አሁን አንድ ልዩ የታሪክ ሂደት ውስጥ እያለፍን መሆኑ ይገባናል፡፡ አሁን እያለፍንበት ያለውን የታሪክ ምዕራፍ በውል ወይም ትምህርት በሚሆን መንገድ ለመረዳት፤ ኢትዮጵያን በታሪክ መነጽር ዘወር ብሎ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም ሆኖ፤ አሁንም ከጀመርነው ፕሮጀክት፤ ከጨበጥነው ድል በላይ ሊሆን ያለው ድልና ወደፊት የሚሰራው ፕሮጀክት ይበልጥ ያጓጓኛል፡፡